https://chilot.me

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፱
አዲስ አበባ ግንቦት ፲፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

23rd Year, No. 39
ADDIS ABABA, 26th May, 2017

**ማውጫ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፭/፪ሺ፱ ዓ.ም

ለሕዝብ ጥቅም መረጃን ይፋ ማድረጊያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ……………………………………….ገጽ ፱ሺ፮፻፵፫

**CONTENT**

Council of Ministers Regulation No.405 /2017

Disclosure of Information for Public Interest Council of Ministers Regulation ………………………………………………... page 9643

የሚኒስትሮች ምክርቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፭/፪ሺ፱

## ለሕዝብ ጥቅም መረጃን ይፋ ስለማድረግ የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፱፻፲፮/፪ሺ፯ አንቀጽ ፭ እና በመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር ፭፻፺/፪ሺ አንቀጽ ፴፯(፫) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "ለሕዝብ ጥቅም መረጃን ይፋ ማድረጊያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፬፻፭/፪ሺ፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

Council of Ministers Regulation No. 405/2017

## COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR DISCLOSURE OF INFORMATION FOR PUBLIC INTEREST

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No.916/2015 and Article 37 (3) of the Freedom of the Mass Media and Access to Information Proclamation No.590/2008.

## PART ONE

## General

### 1. Short Title

This Regulation may be cited as the “Disclosure of Information for Public Interest Council of Ministers Regulation No. 405/2017”.

https://chilot.me



## ፪. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ:-

፩/ "ለሕዝብ ጥቅም ይፋ የተደረገ መረጃ" ማለት በዚህ ደንብ የተደነገገውን በመከተል በቅን ልቦና ይፋ የተደረገ መረጃ ሲሆን ይፋ በተደረገ መረጃ ላይ በሚደረጉ የምርመራ ሂደቶች የተሰጠ ማንኛውንም እገዛ ያካትታል፤

፪/ "የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም" ማለት በአዋጅ ቁጥር ፪፻፲፩/፲፱፻፺፪ የተቋቋመ ተቋም ነው፤

፫/ "የበላይ ኃላፊ" ማለት አንድን የመንግስት ተቋም በበላይነት ለመምራት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ሰው ነው፤

፬/ "ሠራተኛ" ማለት የመረጃ ደህንነት አገልግሎት ሠራተኛን ሳይጨምር ማንኛውም የፐብሊክ ሰርቪስ እና የመንግስት የልማት ድርጅት ሠራተኛ ነው፤

፭/ "የሚመለከተው አካል" ማለት በዚህ ደንብ አንቀጽ ፮ መሠረት መረጃ ይፋ የሚደረግለት አካል ነው::

## ፫. የተፈፃሚነት ወሰን

፩/ ይህ ደንብ የሥራ ግዴታን በመተላለፍ የሕዝብ ጤንነትንና ደህንነትን፣ የአካባቢያዊ ደህንነትን እና ጎጅ የሆነ ከባድ አደጋን በሚመለከት ለሕዝብ ጥቅም ይፋ በተደረገ መረጃ እና መረጃውን ይፋ ባደረገ ሠራተኛ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል::

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (፩) የተደነገገው ቢኖርም ይህ ደንብ የሀገር መከላከያ ሠራዊትን፣ የፖሊስ ሠራዊትን እና የመረጃ ደህንነት አገልግሎትን በሚመለከት መረጃ ላይ ተፈፃሚ አይሆንም::

## 2. Definition

In this Regulation unless the context requires otherwise:

1/ "public interest disclosure" means a disclosure of information made in good faith in accordance with this Regulation and includes any assistance or information given during an investigation on the basis of the disclosure;

2/ "Institution of the Ombudsman" means the Ethiopian Institution of the Ombudsman established under Proclamation No. 211/2000;

3/ "head of a public body" means an official who has been authorized by law to lead any government institution;

4/ "employee" means any person who works for the public service or public enterprise excluding the national intelligence service personnel;

5/ "concerned public body" means a body to which information is disclosed pursuant to Article 6 of this Regulation.

## 3. Scope of Application

1/ This Regulation shall apply to any public interest disclosure concerning a serious danger posed to the health or safety of the public, the environment or any other harmful act committed in violation of duty and on the employee who discloses such impropriety.

2/ Notwithstanding to the provision of sub-article (1) of this Article, these Regulations shall not apply on information concerning to the national defense force, police force and national intelligence service institutions.

https://chilot.me



## ክፍል ሁለት

## መረጃ ይፋ ስለሚደረግላቸው አካላት

### ፬. መረጃን ይፋ ስለማድረግ

፩/ ማንኛውም ሠራተኛ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፫(፩) የተሸፈኑ ጉዳዮችን በተመለከተ ለሕዝብ ጥቅም መረጃን ይፋ ማድረግ ይችላል፡፡

፪/ ለሕዝብ ጥቅም መረጃ ይፋ ያደረገ ሠራተኛ ማንነት በምስጢር መጠበቅ አለበት፡፡

### ፭. መረጃን ለበላይ ኃላፊ ይፋ ስለማድረግ

፩/ ለሕዝብ ጥቅም መረጃን ይፋ የሚያደርግ ማንኛውም ሠራተኛ መረጃውን በቅድሚያ የሥራ ግዴታ መተላለፍ ድርጊቱ ተፈፅሟል ለተባለበት የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ ወይም እርሱ ለወከለው ሰው ይፋ ማድረግ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ቢኖርም በሚከተሉት ሁኔታዎች ለሕዝብ ጥቅም መረጃን በቀጥታ ለሚመለከተው አካል ይፋ ማድረግ ይቻላል:-

ሀ) ማስረጃ ሊደበቅ ወይም ሊጠፋ ይችላል የሚያሰኝ ምክንያታዊ ጥርጣሬ ሲኖር፣ ወይም

ለ) ይፋ የሚደረገው መረጃ አጣዳፊ ጉዳይን የሚመለከት ሲሆን፡፡

፫/ ሠራተኛው የሕግ ምክር አገልግሎት ለማግኘት ለሕግ ባለሙያ መረጃ ይፋ ማድረጉ ለበላይ ኃላፊ የማቅረብ ግዴታውን እንዳልተወጣ አያስቆጥረውም፡፡

፬/ ሠራተኛው መረጃን ለመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ ይፋ አድርጎ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ በበላይ ኃላፊው የመፍትሔ እርምጃ ካልተወሰደ ወይም በተሰጠው ውሳኔ ካልረካ መረጃውን ለሚመለከተው አካል ይፋ ማድረግ ይችላል፡፡

## PART TWO

## Channels of Public Interest Disclosure

### 4. Disclosure

1/ Any employee may, in the interest of the public, make disclosure of information on matters covered under Article 3(1) of this Regulation.

2/ The identity of an employee who makes disclosure of information in the interest of the public shall be kept confidential.

### 5. Disclosure of information to Head of a Public Body

1/ Any employee shall first make a public interest disclosure to a head of the public body where the impropriety is alleged to have been committed or to a person delegated by him.

2/ Notwithstanding the provision of sub-article (1) of this Article, a public interest disclosure may be made directly to the concerned public body where:

a) there is a reason to believe that it is likely that evidence relating to the impropriety will be concealed or destroyed; or

b) the disclosure made is related to a very urgent matter.

3/ An employee who disclosed information to a legal counselor with an intention of seeking legal advice may not be considered as defying his disclosure obligation to the head of the public body

4/ An employee may make public interest disclosure to the concerned public body where the head of the public body to which disclosure is made has not taken action within a reasonable period or the employee is dissatisfied with the decision.

https://chilot.me



**፮. መረጃን ለሚመለከተው አካል ይፋ ስለማድረግ**

መረጃ ይፋ የሚደረገው ለሚከተሉት የመንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች ይሆናል:-

፩/ መረጃው ከግለሰብ ወይም ከሕብረተሰብ ጤናና ደህንነት ጋር የተገናኘ ከሆነ ለጤና ጥበቃ ሚኒስትር፤

፪/ መረጃው ከአካባቢ ደህንነት ጋር የተገናኘ ከሆነ ለአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስትር፤

፫/ መረጃው ጎጅ የሆነ ከባድ አደጋን በአገር ላይ ማድረስን የሚመለከት ሲሆን እንደነገሩ አግባብ ላለው ለሚመለከተው የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ፡፡

**፯. መረጃን ለመገናኛ ብዙሀን ይፋ ስለማድረግ**

በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፮ መሠረት መረጃን ለሚመለከተው አካል ይፋ ያደረገ ማንኛውም ሠራተኛ የመንግስት አካሉ የበላይ ኃላፊ በጉዳዩ ላይ በ፲፭ ቀናት ውስጥ ምርመራ ካልጀመረ ወይም ምርመራ ላለማድረግ ከወሰነ ጉዳዩን ለመገናኛ ብዙሃን ይፋ ማድረግ ይችላል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**ለሕዝብ ጥቅም ይፋ የተደረገ መረጃን ስለመቀበል፤ ስለመመርመር እና ውሳኔ ስለመስጠት**

**፰. ይፋ የተደረገ መረጃን የመቀበልግዴታ**

፩/ በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ እና ፮ መሠረት ለሕዝብ ጥቅም ይፋ የተደረገን መረጃ የመቀበል ኃላፊነት የተሰጠው የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ መረጃውን የመመዝገብ፣ ስለመቀበሉ ማረጋገጫ የመስጠት እና በሚስጢር የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

**6. Disclosure of Information to a Concerned Public Body**

A public interest disclosure shall be made to the following concerned officials of the public bodies:

1/ if the disclosure is related to the health or safety of an individual or the public, to the Minister of Health;

2/ if the disclosure is related to the well-being of the environment, to the Minister of the Environment, Forest Development and Climate Change;

3/ if the disclosure is related to any other serious danger, to the head of the appropriate public body.

**7. Disclosure of Information to the Mass Media**

Any employee, who made a public interest disclosure in accordance with Article 6 of these Regulations, may make the disclosure of information to the mass media where the head of a concerned public body has failed to commence an investigation within 15 days or decided not to investigate the impropriety.

**PART THREE**

**Receipt, Investigation and Decision-Making of Public Interest Disclosure**

**8. Duty to Receive Public Interest Disclosure**

፩/ The head of any public body who is in charge to receive public interest disclosure in accordance with Articles 5 and 6 of this Regulation shall register the information, give to the employee acknowledgement of receipt in writing and keep the record confidential.

https://chilot.me


፪/ ይፋ የተደረገው መረጃ ቢያንስ የሚከተሉትን ማካተት አለበት:-

ሀ) መረጃውን ይፋ ያደረገው ሠራተኛ ሙሉ ስም፣ አድራሻ እና ሥራ፤

ለ) የተፈፀመውን የሥራ ግዴታ መተላለፍ ድርጊት ባጭሩ፤

ሐ) ድርጊቱን ፈፅሟል የተባለውን ሰው ስም እና አስፈላጊ መረጃዎች፤

መ) ከተቻለ ድርጊቱ የተፈጸመበትን ጊዜ እና ቦታ፤

ሠ) በሠራተኛው እጅ የሚገኙ ማስረጃዎች ዝርዝር።

9. <u>ምርመራ ስለማካሔድ</u>

፩/ ይፋ የተደረገ መረጃን ለመቀበል በዚህ ደንብ አንቀጽ ፭ እና ፮ መሠረት ሥልጣን የተሰጠው የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ መረጃው እንደደረሰው ምርመራውን ወዲያውኑ መጀመር አለበት።

፪/ ለሕዝብ ጥቅም መረጃ ይፋ የተደረገለት የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ ለምርመራው ሂደት ጠቃሚ ነው ብሎ የሚያምንበትን ማስረጃ ከማንኛውም ሰው ሊጠይቅ ይችላል።

፫/ መረጃውን ይፋ ያደረገው ሠራተኛ በምርመራው ሂደት የመተባበርና የምርመራውን ውጤት የማወቅ መብት አለው።

፬/ መረጃ ይፋ የተደረገለት የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ ጉዳዩ በሥልጣኑ ስር የማይወድቅ ከሆነ መረጃውን ለሚመለከተው አካል በማስተላለፍ ይህንኑ መረጃ ይፋ ላደረገው ሠራተኛ ማሳወቅ አለበት።

2/ The disclosure of information shall contain at least the following particulars:

a) the full name, address and occupation of the employee who made the disclosure;

b) the nature of the impropriety;

c) the name and particulars of the person alleged to have committed the impropriety;

d) the time and place where the alleged impropriety took place, if possible;

e) any additional evidence under the possession of the employee.

9. **<u>Investigation</u>**

1/ The head of any public body who is authorized to receive public interest disclosure in accordance with Articles 5 and 6 of these Regulations shall immediately commence investigation upon receipt of information.

2/ The head of any public body who received public interest disclosure may require evidence necessary for the investigation from any person who is in control of such evidence.

3/ Any employee who made public interest disclosure has the right to assist during the investigation and know its outcome.

4/ If the disclosed information does not fall under his jurisdiction, the head of any public body shall immediately refer the disclosed information to the concerned public body and notify same to the employee who made the disclosure.

https://chilot.me
https://chilot.me



**፲. ውሳኔ ስለመስጠት**

፩/ ለሕዝብ ጥቅም ይፋ የተደረገን መረጃ የተቀበለ የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ ምርመራውን እንዳጠናቀቀ ወዲያውኑ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት የተሰጠ ውሳኔ ድርጊቱ ተፈጽሟል ለተባለበት የመንግስት አካል መሰጠት ይኖርበታል፡፡

**ክፍል አራት**

**ለሕዝብ ጥቅም መረጃን ይፋ ላደረገ ሠራተኛ ጥበቃ ስለሚደረግበት ሁኔታ**

**፲፩. ጥበቃ የሚደረግበት ሁኔታ**

መረጃ ለሕዝብ ጥቅም ይፋ እንደተደረገ ተቆጥሮ ማንኛውም ሠራተኛ በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ጥበቃዎች ሊያገኝ የሚችለው የሚከተሉትን ሁኔታዎች ሲያሟላ ነው፤

፩/ መረጃውን ይፋ ያደረገው በቅን ልቦና ከሆነ፤

፪/ መረጃውን ይፋ ያደረገው በዚህ ደንብ መሠረት ሥልጣን ለተሰጣቸው አካላት ከሆነ፣ እና

፫/ የራሱን ማንነት እና ይፋ ያደረገውን መረጃ በሚስጥር ከጠበቀ፡፡

**፲፪ ከተጠያቂነት ነጻ ስለመሆን**

ለሕዝብ ጥቅም መረጃን ይፋ ያደረገ ማንኛውም ሠራተኛ በመገናኛ ብዙሀንና በመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር ፭፻፺/፪ሺ አንቀጽ ፴፱ መሠረት የወንጀል፣ የፍትሐ ብሔር እና/ወይም የአስተዳደራዊ ተጠያቂነት አይኖርበትም፡፡

**፲፫ የማስረዳት ሸክም**

ለሕዝብ ጥቅም መረጃ ይፋ ያደረገ ማንኛውም ሠራተኛ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ የማስረዳት ሸክሙ አቤቱታ የቀረበበት ሰው ላይ ይሆናል፡፡

**10. Decision-making**

1/ The head of any public body who received public interest disclosure shall give decision immediately upon the completion of an investigation.

2/ The decision made in accordance with sub-article (1) of this Article shall be given to the public body where the impropriety is alleged to have been committed.

**PART FOUR**

**Protection to an Employee Who Makes Public Interest Disclosure**

**11. Conditions of Protection**

Any employee who makes public interest disclosure shall enjoy protection specified under this Regulation where he:

1/ makes the disclosure in good faith;

2/ makes the disclosure to the public body authorized in accordance with these Regulations; and

3/ maintains the confidentiality of his identity and the disclosed information.

**12. Immunity from Liability**

No employee shall be liable to criminal, civil and/or administrative proceedings for making a public interest disclosure in accordance with the provisions of Article 39 of the Freedom of the Mass media and Access to Information Proclamation No.590/2008.

**13. Burden of Proof**

Where an employee who makes public interest disclosure lodge a complaint, the burden of proof lies on the person against whom the complaint is made.

https://chilot.me
https://chilot.me



**፲፬. ከበቀል እርምጃ ስለመጠበቅ**

፩/ መረጃን ለሕዝብ ጥቅም ይፋ ባደረገ ሠራተኛ ላይ የበቀል እርምጃ መውሰድ የተከለከለ ነው፡፡

፪/ ለዚህ ደንብ አፈፀፀም የበቀል እርምጃ ማለት ሠራተኛው ለሕዝብ ጥቅም መረጃ ይፋ በማድረጉ ምክንያት በመንግስት አካል የሚወሰድ የዲሲፕሊን እርምጃ ሲሆን የሚከተሉትን ያካትታል፣

ሀ) ከሥራ ማባረር፣ ማገድ ወይም ከደረጃ ዝቅ ማድረግ፤

ለ) ያለሠራተኛው ፍላጎት ማዛወር ወይም የሚገባውን ዝውውር መከልከል፤

ሐ) የሥራ ዕድገት ወይም የሥልጠና ዕድል መከልከል፤

መ) ጥቅማጥቅም መከልከል፤ ወይም

ሠ) በሠራተኛው ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ማንኛውንም እርምጃ መውሰድ፡፡

**፲፭. ቅሬታ ስለማቅረብ**

፩/ ለሕዝብ ጥቅም መረጃ ይፋ ያደረገ ማንኛውም ሠራተኛ የበቀል እርምጃ ከተወሰደበት ቅሬታውን ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የቀረበለትን ቅሬታ አጣርቶ አቤቱታውን በተቀበለ በ፴ ቀናት ውስጥ ተገቢውን ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡

፫/ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በሠራተኛው ላይ የበቀል እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ካረጋገጠ እርምጃውን የወሰደው የመንግስት አካል ሠራተኛውን ወደነበረበት የሥራ ሁኔታ እንዲመልሰው ተገቢውን ትዕዛዝ መስጠት ይኖርበታል፡፡

**14. Protection against any Retaliatory Measure**

1/ Any retaliatory measure against an employee who made public interest disclosure shall be prohibited.

2/ For the purpose of these Regulations retaliatory measure means disciplinary measures taken by the public body against an employee who made a public interest disclosure and includes the following:

a) dismissal, suspension or demotion;

b) transfer against his will or refusal of transfer when he is entitled;

c) denial of promotion or training opportunities;

d) denial of any employment benefits; or

e) any measure that result in adverse effect on the employee.

**15. Lodging of Complaint**

1/ Any employee who is subjected to a retaliatory measure as a result of his public interest disclosure may lodge his complaint to the Institution of the Ombudsman.

2/ The Institution of the Ombudsman shall, upon investigating the disclosure, take redressing measures within 30 days from the receipt of the complaint.

3/ If the Institution of the Ombudsman proves that a retaliatory measure has been taken against the employee who made the disclosure, it shall give the appropriate order to the public body who took the retaliatory measure to reinstate the employee to his position held prior to such measure.

https://chilot.me
https://chilot.me



## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### ፲፮. ስለሪፖርት

፩/ ለሕዝብ ጥቅም መረጃ ይፋ የተደረገለት የመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ ይፋ የተደረጉ መረጃዎችን ዓይነት፣ ብዛት እና የተሰጡ ውሳኔዎችን በተመለከተ መረጃዎቹ ይፋ በተደረጉለት ፲፭ ቀናት ውስጥ ለሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

፪/ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የደረሰውን ሪፖርት መሠረት በማድረግ የማስተካከያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ያደርጋል።

### ፲፯. ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

### ፲፰. መመሪያ ስለማውጣት

የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ዋና እንባ ጠባቂ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

### ፲፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት ፲፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም**

**ኃይለማርያም ደሳለኝ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር**

## PART FIVE

## Miscellaneous Provisions

### 16. Reporting

1/ The head of any public body that is authorized to receive public interest disclosure shall submit to the Institution of the Ombudsman a report containing the type, number and decisions made on such disclosure within 15 days of its disclosure.

2/ The Institution of the Ombudsman shall, based on the report, shall cause rectification measure to be taken.

### 17. Inapplicable Laws

No regulation, directive or customary practice shall, in so far as it is inconsistent with the provisions of these Regulations, be applicable with respect to matters provided for in this Regulation.

### 18. Power to Issue Directive

The Chief Ombudsman of the Institution of the Ombudsman may issue directives necessary for the proper implementation of this Regulation.

### 19. Effective Date

This Regulation shall enter into force on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 26th day of May 2017.**

**HAILEMARIAM DESSALEGN**

**PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

https://chilot.me
https://chilot.me

https://chilot.me
https://chilot.me



## የአገልግሎት ክፍያ ሠንጠረዥ

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ዓይነት | የክፍያ መጠን በብር | | |
|---|---|---|---|---|
| | | አዲስ ፈቃድ | ዕድሳት | ምትክ ፈቃድ |
| 1 | የውጭ አገር ዜጎች የሥራ ፈቃድ | 2000 | 1500 | 1200 |
| 2 | የውጭ አገር የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ | 3300 | 3000 | 2700 |
| 3 | የአገር ውስጥ የግል ሥራና ሠራተኛ አገናኝ ኤጀንሲ የሥራ ፈቃድ | 650 | 550 | 450 |
| 4 | የሥራ ውል ማጽደቂያ | 500 | | |



## SCHEDULE OF FEES

| No. | Types of Services | Amount of Fee (Birr) | | |
|---|---|---|---|---|
| | | For New License | For Renewal of License | For Replacement of License |
| 1. | Issuance of Work Permit for Foreigners | 2000 | 1500 | 1200 |
| 2. | Issuance of Overseas Private Employment Agency License | 3300 | 3000 | 2700 |
| 3. | Issuance of Local Private Employment Agency License | 650 | 550 | 450 |
| 4. | Approval of Contract of Employment | 500 | | |

https://chilot.me
https://chilot.me